# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 51 ሚያዚያ 29 2001 ዓ.ም


አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

***ወያኔ የጀመረውን ዘረኛ ጥቃት እንዲያቆም፣ ያሰራቸውን ባስቸኳይ እንዲፈታ፣ ሁሉም የኢትዮጵያ ህዝብና በተለይ የጥቃቱ ሰለባ የሆነው የአማራው ክልል ህዝብ፣ ተማሪው፣ ገበሬው፣ ሠራተኛውና ነጋዴው፣ ወጣቱና አዛውንቱ በተለያዩ መንገዶች ቁጣውን ለመግለጽ መዘጋጀት ይኖርበታል። ......የግንቦት 7 መግለጫ***

***ወያኔ በመከላከያ ያሉትን ስድስት ቅልፍ ቦታዎች ካለምንም ሀፍረት እና ምን ይሉኛል የራሴ ጎጥ በሚላቸው ... ጄኔራል ሳሞራ የነሱ-የጦር ሀይሎች ጠቅላይ አዛዥ፤ሌተና ጄኔራል ታደሰ ወረደ-፤ሌተና ጄኔራል ሳህረ መኮንን ፤ሜጀር ጄኔራል ስዩም ሀጎስ፤ ሜጀር ጄኔራል ገብረ እግዚአብሄር መብራቱ እና ሜጀር ጄኔራል ገዛኢ አበራ ናቸው።ካሉት ሀያ ሶስት ክፍለ ጦሮች የሀያ ሁለቱ አዛዥነት የተያዙት በትግራይ ተወላጆች እንደሆነ ተረጋግጦአል። ከዝግጅት ክፍላችን***

## ወያኔ በዘረኝነት ሰክሮ የሚፈጽመውን ወንጀል ለማስቆም ሁሉም ቆርጦ ይነሣ፡፡

***ከግንቦት 7 ንቅናቄ የተሰጠ መግለጫ***

‹‹መፈንቅለ መንግስት ሙከራ ተደረገብኝ፡፡ ይቅርታ! መፍንቅለ መንግስት ሳይሆን በህዝብ የሚወደዱትን መለስ ዜናዊንና በረከት ሰምኦንን የመሳሰሉ ውድ ባለስልጣኖቼን ሊገድሉብኝ ነበር ›› በሚል ሰበብ ፣ አማራነትን የጥቃቱ ሰለባ አድረጎ ወያኔ በዋንኛነት በአማራ ክልል ውስጥ በመውሰድ ላይ የሚገኘውን ዘረኛ እርምጃ ግንቦት 7 አጥብቆ ይኮንናል፡፡ ሌሎችም ከእዚህ በፊት የተመሳሳይ ጥቃት ሰለባ የሆኑና ወደ ፊትም ተመሳሳይ የሆነ ዘረኛ ጥቃት የተደገሰላቸው መሆኑን የሚያውቁ የተለያዩ ድርጅቶችና የሀገሪቱ ዜጎች በሙሉ ይህን እኩይ ድርጊት ሊኮንኑት ይገባል፡፡

ይህ ዘረኛ ጥቃት አማራነትን ማእከሉ ያደረገ ቢሆንም በአማራነታቸው እየተጠቁ ያሉት የጦር መኮንኖችና የሲቪል ሠራተኞች ያነሱት ተቃውሞ ‹‹በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ጥቂት ዘረኞች የሚፈጸሙት ጭፍጨፋ፣ የመብት ረገጣና ከፍተኛ የሃብት ዘረፋ ያብቃ›› የሚል ነውና ስቃያቸውና መከራቸው ለሁሉም ዜጎች የተከፈለ መስዋእትነት ተደርጎ ሊወሰድ ይገባል፡፡ በተለይ ወያኔ በአደባባይ ሊነግረን ያልፈለገው በአማራነት ላይ ያነጣጠረ ጥቃት እየተፈጸመ የሚገኘው፣ በሺዎች የሚቆጠሩ በሥራ ላይ ያሉና ከዚህ ቀደም ተመሳሳይ ጥያቄ በማንሳታቸው ከሥራ ገበታቸው በግፍ የተቀነሱ ወታደሮችና የሲቪል ሰረታኞች እየታሰሩ፣ እየተቀጠቀጡና እየተሰደዱ ያሉት በወሎ፣ በጎጃም፣ በጎንደር፣ በሰሜን ሸዋና በአዲስ አበባ ከተማ እንደሆነ ለማወቅ ችለናል። በእነዚህ አካባቢዎች የሚኖረውም ህዝብ ይህንን ዘረኛ የሆነ የወያኔ ጥቃት ላመስቆም በአንድነት መነሳት ይኖርበታል፡፡ የወያኔን ዘረኛ ሥርዓት እስከ እለተ ህልፈታቸው በእሽክርና ለማገልግል የቆረቡትን ሆዳም የብአዴን መሪዎች በቃችሁ አጠገባችን አትድረሱ ሊላቸው ይገባል፡፡ ወያኔ የጀመረውን ዘረኛ ጥቃት እንዲያቆም፣ ያሰራቸውን ባስቸኳይ እንዲፈታ፣ ሁሉም የኢትዮጵያ ህዝብና በተለይ የጥቃቱ ሰለባ የሆነው የአማረው ክልል ህዝብ፣ ተማሪው፣ ገበሬው፣ ሠራተኛውና ነጋዴው፣ ወጣቱና አዛውንቱ በተለያዩ መንገዶች ቁጣውን ለመግለጽ መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡

የግንቦት 7 ንቅናቄ በደረሰው መረጃ መሠረት ወያኔ የእርሱን ዘረኛ አገዛዝ ለመፈታተን ወኔው ከሌላቸው ጥቂቶች በስተቀር የተቀሩትን በሠራዊቱ ውስጥ የሚገኙትን አማሮች በሙሉ በአደገኛነት የፈረጃቸው መሆኑን ለማወቅ ችለናል፡፡ በሠራዊቱ ውስጥ ለወያኔ ሥጋና ነፍሳቸውን ሸጠዋል ብሎ ከሚያስባቸው በጣት ከሚቆጠሩ አማሮች በስተቀር በአስር ሺዎች የሚቆጠሩትን የሠራዊቱን አባላት ከማሰር አንስቶ ከሥራ በማባረር የዘር ማጥራት ሥራ ለመስራት ወያኔ ያቀደ መሆኑን ደርሰንበታል፡፡

ይህ እኩይ የወያኔ እቅድ ተፈጻሚ እየሆነ የእያንዳንዱን የጦር መኮንንና ወታደር ቤት ከማንኳኳቱ በፊት ሁላችሁም በግል ይሁን በተናጠል መብታችሁን ላለማስነጠቅ በጊዜ ጥንቃቄ እንድታደርጉ ራሳችሁን፣ ባልደረቦቻችሁንና ወገኖቻችሁን የመከላከል እርምጃ እንድትወስዱ ግንቦት ሰባት ያስገነዝባችኋል፡፡ የወያኔን ከዘረናኛነት የሚመጣ ጨካኝነት አብራችሁ በመስራት የምታውቁት ስለሆነ የተደገሰላችሁ የዘር ማጥራት ሥራ መጨረሻው ምን እንደሚሆን የምትስቱት አይመስለንም፡፡ በታረካችሁ የሌለን ተንበርካኪነት እንደመልካም ሸማ እንድትለብሱ ወኔ ቢስ የአድርባይነት ምክራቸውንና የፈሪ ማስጠንቀቂያቸውን የሚተፉባችሁንና ራሳቸውን አዋርደው የውርደት እድር አባላቸው ሊደርጓችሁ የሚፈልጉትን በሙሉ ‹‹ዞር በሉ ከፊቴ ›› በሏቸው፡፡ ለራሳችሁ መብት፣ ለቤተሰቦቻችሁ፣ ለአከባቢያችሁና ለመላው ኢትዮጵያዊ ወገናችሁ መብት ቁሙ፡፡ ምርጫው በዘረኞቹ ወያኔዎች የዘለላም ባርነት ሥር

(ወደ ገፅ 4 ዞሯል)

## ግንቦት ሰባት ንቅናቄ በአሜሪካን ዋና ከተማ በዋሽንግተን ዲሲ ሚያዚያ 25 2001 ዓ.ም ያካሄደው ስብሰባ በታላቅ ድምቀት ተጠናቀቀ

በዋሽንግተን ዲሲና አካባቢው የሚገኙ የግንቦት ሰባት የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ አባላት ሚያዚያ 25 ቀን 2001 ዓ.ም ታላቅ ህዝባዊ ስብሰባ አካሄዱ። በአካባቢው የሚገኙ አባላት ለውይይት የመረጡት አቢይ ርዕስ ከወያኔ ወድቀት በኋላ ስለሚገነባው ዴሞክራሲያዊ አስተዳደር ሲሆን፣ በስብሰባው ከወትሮው ለየት ባለ ሁኔታ ቁጥራቸው እጅግ በርካታ የሆኑ ኢትዮጵያውያን ተገኝተዋል። የተሰብሳቢው ቁጥር እጅግ ከፍተኛ በመሆኑም አዘጋጆቹ ሁለት አዳራሾችን ለመከራየት መገደዳቸውን ዘጋቢያችን ከስፍራው ሪፖርት አስተላልፏል። በስፍራው በአካል መገኘት ያልቻሉ በተለያዩ አገሮች የሚገኙ በሺዎች የሚቆጠሩ አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ስብሰባውን በኢንተርኔትና በፓልቶክ ተከታትለዋል።

በእለቱ የተሰብሳቢው ስሜት እጅግ የጋለ እንደነበርና ኢትዮጵያውያን ከያሉበት ሆነው ለንቅናቄው ብዙ የገንዘብ ድጋፍ ሲያደርጉ እንደነበር ለማወቅ ተችሏል። በእለቱ ብዙ ገንዘብ እንደተሰበሰበ ሪፖርተራችን የንቅናቄውን የፋይናንስ ሃላፊ ጠቅሶ ከስፍራው ዘግቧል።

ሪፖርተራችን ያነጋገራቸው አንድ ከአዲስ አበባ በቅርቡ የመጡ ሰው እንዲህ ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል “እኔ ከኢትዮጵያ ከመጣሁ ገና አንድ ወር አልሞላኝም። በሀገር ውስጥ በነበርኩበት ጊዜ ስለግንቦት ሰባት ሰምቻለሁ። ብዙ ህዝብም ድርጅቱን በተስፋ እየተጠባበቀው ነው። ቅንጅት ውስጥ ችግር ከተከሰተ ወዲህ ስሜቴ የተጎዳ በመሆኑ እንዲህ ዓይነት ስብሰባ ይደረጋል ብዬ አላሰብኩም ነበር። ዛሬ ባየሁት ነገር በጣም ተደስቻለሁ። በቅርቡ ወደ ኢትዮጵያ እመለሳለሁ። ግንቦት ሰባት እውነትም የወደፊት ተስፋችን እንደሆነ አምኛለሁ። ዛሬ ተስፋዬ ታድሶልኛል። ግንቦት ሰባት ወያኔን ለምን እንዳስደነበረው አሁን ገብቶኛል። እንዲህ ዓይነት ተቀባይነት ያለውና ኢትዮጵያውያንን በዚህ ሁናቴ ያሰባሰበ ድርጅት ሁሌም ወያኔን እንደሚያስደነግጠው ስለማውቅ ተስፋዬ ታድሶልኛል” ብለዋል። (ወደ ገፅ 4 ዞሯል)

## የብአዴን ታጋዮች በተደጋጋሚ አንስተውት የነበረውን የመብት ጥያቄ በማኮላሸት የወያኔ መሪዎችን ላሉበት ትዕቢት ካበቁት ጀሌዎች አንዱ የሆነው የተፈራ ዋልዋ ሚስት በመፈንቅለ መንግሥት ሴራ ተባባሪነት ታስረው እንደተፈቱ ተዘገበ

ወያኔ “በግንቦት 7 ጠንሳሽነት ሊካሄድብኝ ነበር” ባለው የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ እጅግ ከመደናገጡ የተነሳ የቀኝ እጁ የሆነውን የአቅም ግንባታ ሚኒስቴር የተፈራ ዋልዋን ባለቤት ወይዘሮ አይነ ፅጌን ጭምር አስሮ እንደነበር አፍቃሬ ወያኔ የሆነው ሪፖርተር ጋዜጣ በትናንትናው ዕለት ባወጣው ህትመቱ ዘገበ።

ተፈራ ዋልዋ የብሄረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ብአዴን) ታጋዮች ገና ወያኔ በሽግግር መንግሥት ዋዜማ ቁልፍ ቁልፍ የመንግሥት የሥልጣን እርከኖችን መቆጣጠር ከጀመረበት ወቅት አንስቶ በተለያዩ ጊዜያቶች አድርገውት የነበረውን ተቃውሞ በማክሸፍ ለወያኔ በሥልጣን መደላደል ታላቅ ውለታ ከዋሉት ጀሌዎች አንዱ አንደሆነ ሲታወቅ፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአቅምና በችሎታ ማነስ በወያኔ አለቆቹ እየተገፈተረ ተንጠልጥሎ ያለ ሰው እንደሆነ የግንቦት 7 ምንጮች አረጋግጠዋል።

የተፈራ ዋልዋ ባለቤት ወይዘሮ አይነ የታሰሩት የ80 አመት አዛውንት አባታቸው አቶ ፅጌ ሃብተማሪያምን ለመጎብኘት ሂደው ሳለ “ግንቦት 7 አቀነባበረው” በተባለው የመፈንቅለ መንግስት የተከሰሱትን አባታችውን የወያኔ ፀጥታ ሃይሎች ለማሰር በመምጣታቸው ድርጊቱ አግባብ አለመሆኑን በመግለጻቸው እንደሆነ ሪፖርተር በዘገባው ይፋ አድርጓል። ይህን አስገራሚ ዜና የተከታተሉ አንዳንድ ኢትዮጵያዊያን ወያኔ የራሱን ወዳጆች ጠላቴ ከሚላቸው መለየት ተስኖት እንዲህ ዓይነቱን የጅምላ እሥር ማካሄዱ የተዘፈቀበትን ከፍተኛ የስነልቦናና የአካል መረበሽ ያመለክታል ብለዋል። (ወደ ገፅ 4 ዞሯል)

## አንድ የተባበሩት መንግስታት ባለስልጣን በሶማሊያ የተፈጸመውን የጦር ወንጀል የሚመረምር አለማቀፍ ቡድን መመስረት አለበት አሉ

በሶማሊያ የተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ጉዳይ ድርጅት ሃላፊ የሆኑት ሚስተር ጉኢለርሞ ቤቶቺ፥ “ሶማሊያ ውስጥ በጣም አሳሳቢ የሆነ የጦር ወንጀል እና በሰው ልጆች ስብዕና ላይ የሚፈጸም ወንጀል በግጭቱ ተካፋዮች ሁሉ ተፈጽሟል ብዬ በእውነት አምናለሁ፤” ማለታቸውን ሬውተርስ ዘግቧል። ይህንን ወንጀል የፈጸሙትም ህግ ፊት መቅረብ እንዳለባቸው እንደሚያምኑ ገልጸዋል።

ሚስተር ቤቶቺ ጨምረውም፥ በሶማሊ በማናለብኝነት የተፈጸመውን ወንጀል አለም አቀፍ ቡድን ተመስርቶ መመርመር እና የተሰበሰበውን ማስረጃም ለአለማቀፉ የወንጀል ፍርድ ቤት ማስተላለፍ እንዳለበት ለሬውተርስ ተናግረዋል። (ወደ ገፅ 4 ዞሯል)

## ወያኔ ራሱን በውሸት ጠልፎ ሲወድቅ ቆሞ የቀረው እውነት ብቻ ነው

የወያኔ የውሸት ፋብሪካ ሰሞኑን ሥራ በዝቶበታል፤ የገበያውም ሁኔታ ግን ተስፋ አስቆራጭ ነው:: አንዱን የውሸት ምርት ለመደገፍ ሌላ ውሸት መፈብረኩ የሁለቱም ውሸቶች ዋጋ በአስደንጋጭ ሁኔታ እንዲወድቅ አድርጎታል::

የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎትና የፌዴራል ፖሊስ የጋራ ፀረ-ሽብር ግብረ ኃይል ተብየው ለቅዳሜ ሚያዝያ 17 ገበያ ያወጣው ውሸት «በሀገራችን ሠላማዊ ትግል አብቅቷል በማለት የደም ማፋሰስን መንገድ እንደ ብቸኛ የትግል ስልት ያወጀው ራሱን ግንቦት 7 ብሎ የሚጠራውና በውጭ ሀገር በእነ ብርሃኑ ነጋ የተቋቋመው የፀረ-ሠላም ቡድን ሕገ-መንግሥታችንንና ህገ-መንግሥታዊ ሥርዓታችንን በኃይል ለመገርሰስ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር ብር ወጪ በማድረግ የወታደራዊ ንዑስ ቡድንና የሲቪል ንዑስ ቡድን በሚል በሀገር ውስጥ ያደራጀው የሽብር መረብና እንቅስቃሴ በፀጥታ ኃይሎች ከሽፏል» የሚል ነበር::

የኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቪዥንም «የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ከሸፈ!» የአንድ ሣምንት ፈንጠዚያቸዉ ሆኖ ቆየ::

የኢትዮጵያ ሕዝብ ዜናውን በአድናቆት ሰማ፤ ዓለም ዓቀፍ የዜና አውታሮችም አስተጋቡት:: በቀጥታ ባይነገረውም የውስጡም የውጩም አድማጭ የወያኔን ደካማነት እና በጦሩ ውስጥ ያለዉ ተቀባይነትም ዝቅተኛ መሆኑ ማረጋገጫ አገኘ:: በወያኔ መዳፍ ዉስጥ የወደቁትም ከፍተኛ መኮንኖች የአንድ ዘውጌ ማህበረሰብ አባላት መሆናቸዉን እና ከታሳሪዎቹ ዉስጥ ደግሞ እንክብካቤ የሚገባቸዉ የእድሜ ባለፀጎች መኖራቸዉን ሲገለጽ ደግሞ ውሸቱ ዋጋ ከማጣቱም በላይ አውሪውን አቀለለው::

ወያኔ የፈጠረው ውሸት መልሶ ራሱን እንደጎዳው ሲገነዘብ መላ ዘየደ - ሌላ «ደጋፊ» ውሸት መፍጠር:: አርብ ሚያዝያ 23 ቀን በረከት ስምዖን «የግንቦት 7 ንቅናቄ ዓላማ መፈንቅለ መንግሥት ማካሄድ ሳይሆን ባለሥልጣናቶችን መግደል ነበር» አለ:: «ቡድኑ ይህ ነው የሚባል አቅም ያልነበረው ከመሆኑም በላይ የት ቦታ እንዳለ፣ ምን እያደረገ እንደነበር ከመጀመሪያው ጀምሮ ተደርሶበት ነበር» በማለት ቅመም ቢጤ ጨመረበት::

የዜና አዉታሮች ይኽ እርስ በርሱ የሚፋለስን ዜና ለመረዳትም ለመዘገብም እስካሁንም እንደተቸገሩ ናቸው:: ለምንድነው ወያኔ እንዲህ ዓይነቱ ምስቅልቅል ውስጥ የገባው?

በመሠረቱ ወያኔ ውሸቶች ሲዘባረቁበት ይኽ የመጀመሪያ ጊዜው አይደለም:: በምርጫ 97 ማግሥት የቅንጅት መሪዎች ከተከሰሱባቸው ወንጀሎች አንዱ «ዘር ማጥፋት» እንደነበር የሚታወስ ነው:: ይኽ ክስ ከጥቅሙ አሳፋሪነቱ ባሰ:: የትኛዉን ዘር ነዉ ያጠፉት? መቼ ነው ያጠፉት? ምን ኃይል ተጠቅመዉ ነዉ ያጠፉት? ውሸቱ ማለቂያም ምላሽም የሌላቸዉ ጥያቄዎችን ሲያስከትል ክሱ «የዘር ማጥፋት ሙከራ» ተብሎ ይሻሻል ተባለ:: «የዘር ማጥፋት ሙከራ» ምን ማለት እንደሆነ ማንም ሳይተነትነው ተሸፈፍኖ ታለፈ:: በሌላ ወቅትም ይህን ያህል የተራቡ ሰዎች አሉ ካለ በኋላ «በምግብ እጥረት የተጎዱ እንጂ የተራቡ ሰዎች የሉም» ዓይነት ውሉ የጠፋበት ማደናገሪያ ተጠቅሟል:: ያሁኑም ሙከራ እንደዚሁ አደናግሮ ለማለፍ የተወጠነ ቢመስልም በኛ ግምት ከዚህም በላይ የታለመበት ነው::

መፈንቅለ-መንግሥት የሚለዉ ውሸት የወያኔን ደካማነት የሚያጋልጥ ነው፤ ይህ ደግሞ የሆነዉ የመከላከያ ሚኒስትሩ ለፓርላማ ተብዬው የጦሩ በአስተማማኝ ሁኔታ መገኘትና ተደራራቢ ድሎችን ማስመዝገቡን ተፅፎ የተሰጠዉን ካነበበ ጥቂት ሣምንታት በኋላ መሆኑ አሳፋሪነቱን ያጎላዋል:: እስካሁን ከሰማነዉ እንኳን ብንነሳ ጄኔራሎች፣ ኮሎኔሎች፣ ሻለቃዎች እና ሻምበሎች ያሉበት ቡድን አቅም የሌለውና ፈፅሞ ስጋት የሚፈጥር አይደለም ተብሎ የሚታለፍ አይደለም:: ስለሆነም ኃያላን አገሮች የወያኔን ጥንካሬ ጥያቄ ዉስጥ በማስገባት እሱን ተክቶ ከሚመጣዉ ኃይል ጋር አስቀድሞ መተዋወቅን መምረጣቸውን አይቀርም፤ ምልክቶችም ታይተዋል:: ይህ ለወያኔ መርዶ ነዉ::

በሌላ በኩል ግን ባለሥልጣናትን ለመግደልና ተቋማትን ለማውደም የታለመ ነበር ብንል ግንቦት 7ን በሽብርተኝነት ለመክሰስ ያመቸናል ብለው ተስፋ አድርገዋል:: ይህ ተስፋቸው ግን ዋጋ የለውም፤ ጊዜ አልፎበታል:: ግንቦት 7 የሕዝብን ድምፅ ሰርቆ፣ ገድሎና አሰቃይቶ ራሱን በህገ -ወጥ መንገድ ሥልጣን ላይ ያቆየን ዘረኛ አገዛዝን የሚፋለም የነፃነት፣ የፍትህና የዲሞክራሲ ኃይል መሆኑ የዛሬ የወያኔ ወዳጆችም በሚገባ ተረድተዋል::

ወያኔ በራሱ ውሸቶች ይተብተብ እኛ ግን ራሳችንና አገራችንን ነፃ በማዉጣቱ ሥራ ላይ እንበርታ::

በመከላከያ፣ በፓሊስ፣ በደህንት ተቋማት እና በኢህአዴግ ዉስጥ ላላችሁ ነፃነትና ፍትህን ናፋቂ ለሆናችሁ ወገኖቻችን እንዲህ እንላችኋለን:: የወያኔ ዘረኛ አገዛዝ እንዲያበቃ፣ ዜጎች ሁሉ በእኩልነት የሚኖሩባት፣ ነጻነት መብትና ፍትህ የተከበረባት ኢትዮጵያን ለማየት ያላችሁን ህልም አውቀነዋል:: ይህንን ውብና ህዝባዊ ፍላጎት ለማሳካት መከፈል ያለበትን መስዋእትንት ለመክፈል መወሰናችሁን ተረድተናል:: ሰሞኑን ወያኔን አሳፈሪ በሆነ የቅጥፍት ቅሌት ውስጥ የጨመረው፣ ይህ «እምቢ ለዘረኛነት» የሚለው እምነታችሁ እንደሆነ ተረድተነዋል:: ወያኔ «መፈንቅለ መንግስት» ይበለዉ ወይም «መለስ ዜናዊን የመግደል ሙከራ» ዓላማዉ የወያኔ ዘረኛነትን መሸከም በቅቶናል ባሉ የአማራ የጦር መኮንኖች፣ ባለሌላ ማእረግ ወታደሮችና የሲቪል አስተዳደሩ ሰራተኞች ላይ የተነጣጠረ ነው:: ወያኔ ያልገባው ግን በወያኔ አምባገነናዊ ዘረኛነትና ዘራፊነት የተንገፈገፉት የአማራ መኮንኖቸ ብቻ ሳይሆኑ መላው የኢትዮጵያ ህዝብ መሆኑን ነው:: ይህ የጸረ-ዘረኛነትና የጸረ-አምባገነናዊነት ትግል የሁሉም ኢትዮጵያዊ ትግል ነው:: እናንተም መሸከም በጀመራችሁት ህዝባዊ እምነታችሁ ጽኑ::

የመለስ ዜናዊ ወታደሮችና ፖሊሶች ሳይሆን፣ ራሳችሁን የኢትዮጵያ ሕዝብ ሠራዊትና የፖሊስ ኃይል የሚል ሕዝባዊ መጠሪያ የምታጎናጽፉበት ቀን ደርሷል:: በየጦር አውድማው ስትሞቱ አብሯችሁ የሚሞት፣ ስትቆስሉ የሚቆስል፣ ስትደሙ የሚደማ፣ በሃገር አለኝታነት በሕዝብ መከታነት እናንተን ለማየት የናፈቀ ሕዝብ እቅፉን ከፍቶ ይጠብቃችኋል:: እናንተም የመለስን ጸረ- ኢትዮጵያ ዘረኛና አምባገን አገዛዝ ለማስወገድ የኢትዮጵያ ሕዝብ የጀመረዉን ትግል በስፋት ተቀላቀሉ:: ሁላቸንም በአንድነት እየተነሳን ነው:: የመለስ ዜናዊን ዘረኛ ሥርአት ለቀትር ጸሃይ እንደተጋለጠ ቅቤ፣ በአነስተኛ የሃገርና የሕዝብ ኪሳራ ማቅለጣችን ደግሞ አይቀሬ ነው::



የፖስታሳጥን ቁጥር :- POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

ሃይለ ሀሳብ

## በተወዳጁ ኢትዮጵያዊው ጥላሁን ቀብር ላይ ያልተሳካው ሙከራ - የነበረከት ስምኦን ሴራ (የግንቦት 7 ዘጋቢ ከአዲስ አበባ)

ነጋዴ ሲከስር በስጦታ ከስንት ጊዜ በፊት የቸረውን እንደ እዳ ለመሰብሰብ ይሞክራል፡፡ ሙከራው ግን ከንቱ ስለሚሆን ከኪሳራው አይመልሰውም ወይም ገቢ አያመጣለትም፡፡ ጭራሹን ጠላት ማብዛት ነው ትርፉ፡፡ ስጦታ ሰጠን ብለው ሲያመሰግኑት የነበሩት ሁሉ ስጦታው እዳ ሆኖ ሲመጣባቸው ከጥላቻ ሌላ ክፍያ አይኖራቸውም፡፡ በኪሳራ ላይ ኪሳራን ሲከናነብ የከረመው ወያኔም፣ እንደዛው ባገኘው መንገድ ሁሉ ገቢ ለማግኘት ነው ሙከራው፡፡ ትርፍ አመጣ አላመጣ ግድ የለም፤ የአንድ ሰሞን ወሬ እስከሆንና ለቀናት የሕብረተሰቡን ህሊና ለመያዝ እስከበቃ ድረስ፡፡ ነገር ግን ወያኔ ከፉኛ እንደሚጠሉ ስለሚያውቅ አመራሩን ወይም የኔ የሚላቸውን ፊት ለፊት አውጥቶ አያስነግዳቸውም፤ ወይም አያስደልላቸውም፡፡ ለድለላውና ለፍላጎት ማሟያነት የሚጠቀመው ወዶ ገባዎቹን ነው፡፡

የታላቁ ድምጻዊ ጥላሁን ገሰሰ ሕይወት ማለፍ ዜና እንደተነገረ፣ የኢትዮጵያ ህዝብ በብርቅዬ ልጁ ማለፍ ልቡ ተሰብሮ ሃዘን ሲገባ፣ ወያኔ ግን በህዝብ ዘንድ መልካም ገጽታን እንዳገኝ ይረዳኛል ብሎ ያሰበው እድል ስለተፈጠረለት ተደሰተ። ወያኔ በጥላሁን ገሠሠ ላይ ለአመታት የቆየ ቂም አንዳለው ይታወቃል። ከወያኔ ባለስልጣናትም ውስጥ ግን ጥላሁንን እጅግ ከሚጠሉት አንዱና ቂም ይዞበት ስሙ ሲነሳ እንኩዋን የሚያንገሸግሸው ሰው ቢኖር በረከት ስምኦን ነው፡፡ ወያኔ እንደገባ ሰሞን በተደጋጋሚ ጥላሁንንና መሰል ባልደረቦቹን እንደሕዝብ ጠላት እያደረገ በኢቲቪ ያቀርብ ነበር።

የጥላሁን ሞት እንደተነገረ ግን፥ አገዛዙ ሩህሩህ ልብ ባላቸው ሰዎች የተሞላ ለማስመሰል አጋጣሚውን ለርካሽ ፕሮፓጋንዳ ለመጠቀም እንደሚችል ታየው። ወያኔ ለሙታንም ለህያዋንም ክብር ስለሌለው፣ ይህንን ሙከራ ሲያደርግ የሚቹን ቤተሰብ ሊጋፋና ሊያሳዝን እንደሚችል ቢያውቀውም ጉዳይ አልነበረውም። ይህንን ጥንስሱንም ስራ ላይ ያውሉለት ዘንድ፥ የኪነ ጥበብ ስራ ሳይሳካለት በመቅረቱ ወደ ድለላው ገብቶ የሚያንቧችረውን አበበ ባልቻ የተባለ ግለሰብና እና ካቅሙ በላይ አለሁ ባይ የሆነውን ሌላውን ደፋር የወያኔ ጉዳይ አስፈጻሚና የባለስልጣናት አፋሽ አጎንባሽ መቶ ዓለቃ ተስፋዬ ማሞን መለመላቸው። እነዚህ ሁለት ሰዎችም ከሌሎች አጃቢዎች ጋር በታዋቂው ድምጻዊ ቤተሰብ መሃል በመገኘትና ከሼህ ሙሃመድ አላሙዲን የተላከን ነን በማለት፣ ሃዘኑ እንደጎዳቸው መስለው የዛን ታላቅ የሙዚቃ ንጉሥ ታሪክ ለመጉዳት ሽረባቸውን ተያያዙት፡፡

ሰኞ ጠዋት ኮሚቴ መዋቀር አለበት በሚል አጣዳፊ ውትወታ፣ ቤተሰቡ ግራ በተጋባበት ወቅት እራሳቸውን ሰብሳቢ፤ ጸሃፊ፤ የፕሬስ ሃላፊ፤ የሎጂስቲክስ ሃላፊ በማለት ተሰያይመው አንዳንድ ባለሙያ ጓደኞቹን ለስሙ በኮሚቴው አካተው፣ ነገር ግን ምንም ስልጣንና ወሳኝነት እንዳይኖራቸው በማድረግ የመጀመርያ እቅዳቸውን አሳኩ፡፡ ሰኞ እለት በተደረገው ስብሰባ ከተነሱት ነጥቦች መካከል አንዱ የድምጻዊው ንጉስ ልጆች የሚመጡበትን መንገድ ማመቻቸት ሲሆን፤ ቀጣዩ የአበበ ባልቻ ተልእኮ ነበር፡፡

በረከት ስምኦን፥ አበበ ባልቻን «ይህን ታላቅ አጋጣሚ ኢህአዴግ ሊጠቀምበት የሚገባ ነውና አስፈላጊውን ሁሉ ማድረግ አለብህ፤ የሬዲዮ ጣቢያ የሰጠንህ እንዲያው አይደለም፤ ለዚህ ካልሆንከን ለመቼ ልትሆነን?» በማለት መመርያ ሰጥቶታል፡፡ ቅድሚያ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሃዘን መግለጫ ስለሚልኩ ቤተሰቦቹና ወዳጆቹ እንዲሁም የግል ጋዜጣ አሳታሚዎችና ሪፖርተሮች ተሰባስበው እንዲገኙ በማድረግ ደብዳቤው እንደመጣ በአደባባይ ማንበብ እንዳለበት ይነገረዋል። አበበም ወዲያው ሚስጥር ጠብቆ በታዘዘው መሰረት ይፈጽማል፡፡

በዚሁ እለት ስለቀብር ስርአቱ ለመነጋገር በተደረገው ስብሰባ ላይ፥ ቀብሩ ረቡዕ እንደሚሆን፣ ውጪ ያሉትን ጨምሮ ቤተሰቡ በሙሉ ማክሰኞ ተካተው እንደሚገቡ፣ በእለተ ቀብሩ አበበ ባልቻ የፕሮግራም መሪ እንደሚሆንና የሕይወት ታሪኩን ደሞ የዓመታት ጓደኛው፣ ሚዜውና ወዳጁ የሆነው ደበበ እሸቱ እንዲያነበው፣ እንዲሁም ቀብሩ ሥላሴ ካቴድራል እንዲሆን ከጳጳሱ ፈቃድ እንዲጠየቅ አያሌው መስፍንና አብራር አብዶ ይመደባሉ። እነዚሁ ሰዎች አበበ ባልቻን ጨምሮ የማስታወቂያ ሚኒስቴር እንዲተባበር እንዲጠይቁም ይወሰናል፡፡

በዚሁ መሰረት ሁሉም የተሰጠውን ሃላፊነት ለመወጣት ተሰማርቶ እያለ አንድ ሌላ የሃዘን መግለጫ ደብዳቤ ከፕሬዜዳንቱ ቢሮ ስለሚመጣ ሁሉም የኮሚቴ አባላት እንዲሰባሰቡና ልክ የአቶ መለስ ደብዳቤ እንደቀረበው ሁሉ ይህም ጎላ ብሎ እንዲቀርብ ሆኖ ሌላ የፕሮፓጋንዳ ተልእኮ ተፈጸመ፡፡ በዚሁ እለት ደግሞ፥ ኦማር አልበሽር ሃገር ሊጎበኙ ስለሚመጡና ረቡዕ እለትም በርካታ ስምምነቶች የሚፈረሙበት እለት ስለሆነ ቀብሩ ሐሙስ እንዲሆን አቶ በረከት አበበ ባልቻ ቤተሰቡን ሰበብ ፈልጎ እንዲያሳምንና ቀኑ እንዲዛወር አመራር ይሰጠዋል፡፡ በዚሁ መሰረትም አበበ የተነገረውን በኮሚቴው በኩል ያስፈጽማል፡፡ ይህ ውሳኔ ሲተላለፍ፣ ቤተሰቡ ከሰኞ ጀምሮ በድካምና በመከራ ላይ መሆኑ ለበረከት ስምኦን እና ለጉዳይ አስፈፃሚዎቹ ደንታ አልሰጠም፡፡

እንዲህ በእንዲህ እያለ ቀስ በቀስ በኢትዮጵያዊነቱ የሚኮራውን፣ የሚመካውን፣ በአንድነት የሚያምነውን፣ የጦሩ መበተን የእግር ቁስል የሆነበትን የዜማውን ንጉሥ የታላቁን የጥላሁን ገሠሠን ቀብር የፖለቲካ መነገጃ ገበያ ለማድረግ ጉዞው ተስተካክሎ ተቀየሰ፡፡ ማስታወቂያ ሚኒስቴር ደርሶ ሲመለስ አበበ ባልቻ በጣም አሳሳቢ ነው ብሎ በቅድሚያ ለኮሚቴው ያቀረበው ጉዳይ ስለሕይወት ታሪክ መነበብ ነበር፡፡ «እንደምታውቁት በዚህ የቀብር ስርአት ላይ ታላላቅ ባለስልጣናት ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ባለስልጣናት ደግሞ ለታዋቂው ወንድማችን ለጥላሁን ያላቸው ክብርና ፍቅር ያየነው ነው፡፡ አሁንም የጠየቅነው ሁሉ ሊፈቀድልን ነው። እንዲያውም የማስታወቂያ ሚኒስቴር ም/ሚኒስቴር በስብሰባችን ላይ ሊገኙ ስላቀዱ፣ የሕይወት ታሪክ አንባቢ ይሁን ያልነው ደበበ እሸቱ ታሪኩን እንዲያነብ ማድረጉ እነዚህንና ሌሎቹንም ባለስልጣናት ሊያስከፋ ስለሚችል ሌሎች ሰዎች እንዲያነቡት መደረግ አለበት» ይላል፡፡ ደበበ እሸቱ የአንድነት ፓርቲ አመራር አባል መሆኑ ይታወቃል።

ይህን ጉዳይ አብራር አብዶና አዱኛ ቸኮል የተባሉት የሃገር ፍቅር አርቲስቶች «ጨርሶ አግባብነት የሌለው፤ ይህ የፖለቲካ ጥያቄ ሳይሆን ሰብአዊ ግንኙነት በመሆኑ ከፖለቲካ ጋር ሊያያዝ አይገባውም። ደበበ እኮ የረጅም ዘመን ጓደኛው፣ ሚዜው፣ የ60ኛውን ዓመት የጥላሁንን የልደት በዓል ያዘጋጀ ነው፡፡ በግለሰቦች ግንኙነት ላይ ፖለቲካ ምን አገባው?» በማለት ክርክር ይገጥማሉ፡፡ የኮሚቴው ሰብሳቢ አበበ ባልቻና ተስፋዬ ማሞ ጠንክረው ሙግት ይይዛሉ፡፡ «ብዙ ነገር ሊበላሽ ይችላልና ይለወጥ» ብለው አሻፈረን ሲሉ፣ አብራርና አዱኛም ነገሩ ጨርሶ መስመር የሳተና ሊቀበሉት የማይገባቸው፤ እንዲያውም መንግሥትም ሆነ ባለስልጣናቱ ይህን የሚሉ እንደማይመስላቸው አስረግጠው ቢናገሩም፤ አንድ ጊዜ አበበ ሌላ ጊዜ ተስፋዬ አንዱ ላንዱ ምስክር እየሆኑ ይሄ ነገር በአንዳንድ ባለስልጣናት መነሳቱን በመመስካከርና ውሳኔውም የሰብሳቢው መሆን እንዳለበት ሆኖ በዚሁ ይወሰናል፡፡ እጅግ ግራ በሚያጋባና በሚያስገርም ሁኔታም፥ አበበ ባልቻና ተስፋዬ ማሞ አንባቢ ማን ይሁን የሚለውን መንግሥት ይወስናል ብለው ደመደሙ፡፡

ሁለቱ ተቃዋሚዎች፣ አብራርና አዱኛም ብቻቸውን ቀሩ፡፡ ከዚህ በኋላ ማንኛውንም ጉዳይ ሌሎች አባላት እንዲያው እንዲያውቁት ያህል ይነገራቸዋል እንጂ ወሳኞቹ፣ አርቃቂ እና አስፈጻሚ በበረከት ስምኦን የተመደቡት አበበና ተስፋዬ ብቻ ሆኑ፡፡ ረቡዕ ከቀትር በኋላ በ9 ሰአት በተደረገው የኮሚቴ ስብሰባ ላይ የመኪናና የሰው ይለፍ እነማን ማግኘት እንዳለባቸው ተወስኖ ለኮሚቴው ሲነገር፣ አንዳንድ የኮሚቴ አባላት ስም እየጠሩ ይለፍ ሊያገኙ ይገባል ያሉዋቸውን ለሊቀመንበር አበበ ባልቻ አስመዘገቡ፡፡ በዚህ ውስጥም የታዋቂው ድምጻዊ ንጉሥ የቀድሞ ባለቤት ስምና ሌሎችም ተካተው ነበር፡፡

ቀደም ብሎ የሕይወት ታሪኩን የሚያነብ መሆኑ ለአርቲስት ደበበ ተነግሮት ስለነበር፣ አሁን መለወጡን ማን ይንገረው የሚለው ጉዳይ ግራ ቢያጋባም በዚህ እለት በአብራር በኩል እንዲነገረው ተደረገ፡፡ ሐሙስ ጠዋት ይህ ጉዳይ ለደበበ ሲነገረው በአካባቢው የነበረ ሰው፥ ደበበ ስቆ «አይይ ርካሽነት! መንግሥት ያላሰበውን ምን ለማግኘት እንዲህ አይነት ሰበብ ተፈጠረ? እኔስ ግድ የለም ግን መንግሥት ይህን ሰምቶ እንዳይታዘባችሁ» ብሎ ማለፉን ነገረኝ፡፡

በተገባው የኮሚቴው ቃል መሰረት ቃል የተገባላቸው ሁሉ ወደ ልቅሶው ቤት በመሄድ አበበ ባልቻ የታተመውን የይለፍ ወረቀት እንዲሰጣቸው ቢጠብቁ፣ አበበ የለም፡፡ ቀሪ የኮሚቴ አባላትም ያለበትን አያውቁም፡፡ የጥላሁን ልጆች እናትን ጨምሮ በርካታ የቤተሰብ አባላት ቤተሰቦቻቸውን፣ በተለይ አቅመ ደካማ የሆኑትን፣ ወደ መስቀል አደባባይና ሥላሴ ለማድረስ እንዲችሉ ፈቃዱን ቢጠብቁ የለም፡፡ አበበ የይለፍ ፈቃዱን ካሳተመው ሰው ተረክቦ ጠቅልሎ ይዞት ሄዷል ተባለ፡፡ በመጨረሻም አብራር ለአበበ ደውሎ «ሰው እየጠበቀ ነው፤ ቤተሰብም ይለፍ ለመውሰድ መጥቶ ይጠብቃል» ቢለው፣ አበበ የሰጠው መልስ አጭር ነበር፡፡ «እኔ በመመርያው መሰረት ይለፌን በሙሉ ለአቶ በረከት ስምኦን ሰጥቻለሁ» የሚል፡፡ አብራርም፥ "ምን አገባቸው? ምንስ ያደርግላቸዋል? ለሚኒስትሮች ተብሎ 20 ነው የተጠየቀው፤ አንተ ደግሞ መቶውንም ይዘህ ነው የሄድከው እና ሌላው ቢቀር የጥላሁን ልጆች እናቶች በምን ይለፉ?» ቢለው፤ አበበ በድፍረትና በብልግና «ቢፈልጉ በእግራቸው ይሂዱ» ብሎ ዘጋ። ከዚያ በኋላ ቢሞከርም ስልኩ ጠፍቷል ሆነ መልሱ፡፡ በርካታ የቤተሰቡ አባላት በሁኔታው በመገረምና በንዴትም ጭምር «ቀብሩንም ሳይከለክሉን ብንሄድ ይሻላል» በሚል ስሜት ወደየቤታቸው፣ ገሚሱም የጉዞውን መጀመር ሲጠብቅ ለመቆየት መንገድ ገባ፡፡

በመስቀል አደባባይ ያለው ሕዝብ ገና ከመንጋቱ ነበር ቦታ ለመያዝ የደረሰው፣ ሌሎችም ቦታ እየያዙ ነው፡፡ አልፎ አልፎ ወጣቱ በልቡ ያለውን ቁጭት በዚህ እለተ ቀብር ሽኝት ላይ ለማንሳት መሞከሩ አልቀረም፡፡ «ቴዲ እግዚአብሔር ያጥናህ»፣ «ይብላኝ ላንተ ቴዲ፤ እኛስ ልንሰናበተው ነው» «አንተን አስሮ ለጥላሁን ቀብር ሸር ጉድ» እና የመሳሰሉ አስተያየቶችን ሲሰጡ ስለነበር፣ ፖሊስ ደግሞ በዚያው በመስቀል አደባባይ ባለው የሚስጥር መቀጥቀጫውና አስሮ ማንገላቻው ቦታ እየወሰደ አንዳንዶቹን ቀጥቅጦ እስከ መጨረሻው አስሮ አውሏቸዋል፡፡ ያም ሆኖ አልቀረም ስሜት ተገልጾ ምሬትም ተነግሮበታል፡፡

አስከሬኑ በ6 ሰአት መስቀል አደባባይ ይደርሳል ተብሎ ፕሮግራም የወጣለት ቢሆንም፣ ሳይታሰብ ቦሌ መንገድ ላይ አስከሬኑ ከወጣበት ከመኖርያ ቤቱ ጥቂት እንደተጓዘ የጥላሁን ልጆች እናት ወ/ሮ ማርታ፣ ጠዋት አበበ ባልቻ ሲጠየቅ "ቢፈልጉ በእግራቸው ይሂዱ" ብሎ የይለፍ ፈቃድ የከለከላቸው፤ መንገዱ ላይ ጠብቀው አስከሬኑ ሰን ሻይን ሕንጻ አጠገብ ሲደርስ እሪ እያሉ የአስከሬን መኪናው ፊት ለፊት በመቆምና መኪናውንም በማቆም «ልጆችህን ምን ልበላቸው ጥላሁን? አውቃለሁ አንተ እኮ መጥፎ ሰው እንዳልሆንክ፣ አውቃለሁ ጥላሁን! የፈራሁት ይህንን ነበር እኮ!» በማለት በቤተሰቦቻቸው ታጅበው እያነቡ ጮሁ፡፡ «እዬዬ! ምን ሊረባህ ጥላሁን፤ እንዳላጅብህ እንዳልቀብርህ ሊከለክሉኝ ሞከሩ እኮ ጥላሁን! ልጆችህን ማለፊያ አልሰጥም አሏቸው እኮ!» እያሉ ምሬታቸውን አሰሙ፡፡ በመጨረሻም አበበና ተስፋዬ ማሞ ስለሌሉና ቀሪ የኮሚቴው አባላትም አቅም ስላጡና በአካባቢው የነበረውም ሕዝብ «እውነታቸውን ነው፤ የተደረገው ልክ አይደለም የሙት ዓምላክ ይፍረዳቸው» በማለት ከወ/ሮ ማርታ ጋር በመወገኑ ሳይወዱ መኪና ሰጥተው ቤተሰቡን ወደ መስቀል አደባባይ እንዲሄድ አደረጉ፡፡

በዚህና ባልተስተካከለ የኮሚቴ ሸር ጉድ አስከሬኑ በተባለበት ሰአት ሳይሆን ዘግይቶ በ7 ሰአት ከ10 መስቀል አደባባይ ደረሰ፡፡ ሕዝቡ በእንባ ተራጨ! ሃዘኑን በመሪር ስሜት ገለጸ፡፡ በዚህ ቦታ ላይ ነው በወያኔ ትእዛዝና በአበበ ባልቻ አጋፋሪነት የተመደበው የሕይወት ታሪክ አንባቢና የኢሕአዴግ አባል፣ የሚሌኒየም የአዲስ አበባ ሹመኛው ኪሮስ ኃይለስላሴ በዘር ምርጥነት የተመደበ መሆኑ የታየውና በሕዝቡ ላይ የመጀመርያ ቅሬታ ያሳደረው፡፡ በዚህ ላይ ደግሞ ቀደም ሲል ተልኮ የነበረው የፕሬዜዳንቱ የሐዘን መግለጫ ሲነበብና በሌላ ብሀረሰብ ቋንቋ መዝፈን በተከለከለበት ዘመን በኦሮምኛ ዘፍኗል የሚል በኢትዮጵያ ውስጥ በሌላ ብሄረሰብ ቋንቋ መዘፍን ከወያኔ አገዛዝ በፊት የተከለከለ አንደነበር የሚገልጽ የወያኔ ደረቅ ውሸትና ዘረኝነት የሚረጭ አረፍተ ነገር ሲነበብ ሕዝቡ በጉርምሩምታ ቅሬታውን ማሰማት ጀመረ፤ ደግነቱ ቶሎ በረደ፡፡ በመስቀል አደባባይ ስርአቱ ሲካሄድ ቆይቶ ቀብሩ ወደሚፈጸምበት ሥላሴ ካቴድራል ለመሄድ አስከሬኑ ሲንቀሳቀስ አጅበው ከሚሄዱት መሃል ፖሊስ አንዳንድ ወጣቶችን በመጠቋቆም እያወጣ ወደ ሰዋራው ቦታ ያስገባቸው ነበር፡፡ አንዲት ወጣት ሴት ልጅ በፖሊስ ተይዛ በያዙት ቆመጥ መተዋት ፒካዴሊ ቡና ቤት በረንዳ ላይ መሄድ አቅቷት ስቃይ ላይ ስለነበረች ባካባቢው የነበሩ በረዶ አርገው አሸተውላት በመከራ እንባዋን አደረቁላት፡፡

በቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ደግሞ ሁለተኛው የኢሕአዴግ አባልና የአበበ ባልቻ ሬዲዮ ኤፍ ኤም አባል የሆነው ተፈሪ ዓለሙ፣ ያውም ለጥላሁን ጭራሽ ፍቅርም ሆነ ከበሬታ ያልነበረው ሰው፣ የሕይወት ታሪክ አንባቢ ሆኖ ብቅ አለ፡፡ የዘለአለማዊው ጥላሁን ገሠሠ ቀብር መድመቁ ኢሕዴግ ስላደረገው ሳይሆን፣ አበበ ባልቻ ስላጣመመው ሳይሆን፤ ሕዝብ ፈቅዶ አለመመርያና ትእዛዝ በስሜቱ ብቻ ፍቅሩን ለመግለጽ በመውጣቱና በመልካም ሥራው ብቻ ነው፡፡ **(ወደ 4ኛው ገፅ ዞሯል)**

## ወያኔ በዘረኝነት ሰክሮ የሚፈጽመውን ወንጀል ለማስቆም

(ከግፅ 1 የዞር)

መውደቅ ወይም ሞት ከሆነ ደግሞ ሞትን ሺ ጊዜ እንድምትመርጡ ነጻነትን ለማያውቁት ነጻ አውጪዎች በተግባር አሳይዋቸው፡፡ የግንቦት 7 ንቅናቄ ለእናንተና እንደ እናንት «አምቢ ለመብቴ! እምቢ ለነጻነቴ!» በማለት በየትኛውም የሃገሪቱ ክፍል ከሚነሳ ወገናችን ጎን ሁሌም ይቆማል፡፡ በሚቻለው ሁሉ የኢትዮጵያ ህዝብ «እምቢ ለዘረኛ አምባገነኖች! እምቢ ለዘራፊዎች!» በማለት ለሚያደርገው ትግል ግንቦት 7 ሙሉ ድጋፉን ይሰጣል፡፡

በእዚህ አጋጣሚ ይህ ከቁጥጥር ውጭ በመውጣት ላይ የሚገኝን፣ መለስ ዜናዊና ጥቂት ዘረኞች ህዝብን በዘር እየለዩ የሚወስዱትን የማጥቃት እርምጃ፣ ይህ ድርጊት ለዘመናት አብሮ በኖረ ህዝብ መካከል ጥሎ የሚያልፈውን ቂም የምትገነዘቡ በዘረኛነት ያልተለከፉችሁ የሀገር መከላከያ ሠራዊት አባላት፣ የወያኔ ፖለቲካ ድርጅት አባላት እንዲሁም ሌሎች የትግራይ ልጆች ይህን የዘር ማጥራት ተግባር በግልጽና በአደባባይ እንዲኮንኑ ጥሪ እናቀርባለን፡፡ ጥቂት የወያኔ ባለስልጣናት በወያኔ አባላት ስም በጦር ወንጀልና በዘር ማጥፋት የሚያስጠይቅ ዘግኛኝ ወንጀል እየፈጸሙ፣ አሁንም በእዚሁ የጥፋት ጎዳና ሲነጉዱ « በእኛ ስም አይደረግም» የሚል ተቃውሞን አለማሰማት በዝምታ በተደረገ የተባበሪነት ወንጀል የሚያስጠይቅ መሆኑን ወቅቱ ሳይረፍድ ልናስታውሳቸው እንወዳለን፡፡

ግንቦት ሰባት የፍትሕ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ
ሚያዚያ 27/2001 ዓ.ም

## ግንቦት ሰባት ንቅናቄ በአሜሪካን ዋና ከተማ በዋሽንግተን ዲሲ

(ከገፅ 1 የዞረ)

በእለቱ ከግንቦት ሰባት አመራር አባላት መካከል የንቅናቄው ሊቀመንበር ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ እና የንቅናቄው የውጭ ግንኙነት ሃላፊ አቶ ኤፍሬም ማዴቦ ጽሑፍ ያቀረቡ ሲሆን፤ ከንቅናቄው ውጭ ደግሞ የቀድሞ የደቡብ ክልል የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕረዝዳንትና ከግንቦት ሰባት ምርጫ በኋላ በኢትዮጵያ የተፈጠረውን ቀውስ እንዲያጣራ የተቋቋመው አጣሪ ኮሚሽን ሊቀመንበር የነበሩት ዳኛ አቶ ፍሬህይወት ሳሙኤል ጥናታዊ ጽሑፋቸውን አቅርበዋል።

አቶ ኤፍሬም ማዴቦ "የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ እና የግብረገብ እና የባህል ግብዓቶች" በሚል ርዕስ፣ ዳኛ ፍሬህይወት ሳሙኤል ደግሞ፥ "የህግ የበላይነት የዴሞክራሲ ስርዓት የማዕዘን ድንጋይ" በሚል ርዕስ፤ እንዲሁም ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ፥ "ካለፉት ስህተቶች ተምረን ለዘላቂ ዲሞክራሲ ምንና እንዴት ማድረግ አለብን?" በሚል ርዕስ ጽሁፍ አቅርበዋል።

አቅራቢዎቹ ንግግራቸውን ካጠናቀቁ በኋላ ከስብሰባው ታዳሚዎች ጋር እጅግ ገንቢ የሆነ የጥያቄና መልስ እና የውይይት ጊዜ አሳልፈዋል። በስብሰባው ማጠናቀቂያ ላይ "ግንቦት ሰባት እኔ ነኝ" በሚል ርዕስ አንድ ግጥም የተነበበ ሲሆን፣ የተሰብሳቢውን የሀገር ፍቅር ስሜት ስለቀሰቀሰው በርካቶች የደስታ እንባ ከአይናቸው ሲያፈሱ እንደነበረ ለማወቅ ተችሏል።

### አንድ የተባበሩት መንግስታት ባለስልጣን በሶማሊያ የተፈጸመውን የጦር ወንጀል

(ከገፅ 1 የዞረ)

የኢትዮጵያው አገዛዝ ወደ ሶማሊያ ጦሩን ከላከ በኋላ በተቀሰቀሰው ውጊያ፥ ቢያንስ አስር ሺህ ንጹሃን ሶማሊዎች እንደሞቱ፣ የባህር ላይ ዘረፋ እንደተባባሰ፣ እና ከሚሊዮን የሚበልጡ ሶማሊዎች ከመኖሪያቸው እንደተፈናቀሉ የዜና አውታሩ ጨምሮ ገልጿል።

እንደ ሂውማን ራይትስ ዎች እና አምነስቲ ኢንተርናሽናል ያሉ አለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ተቋማት በሶማሊያ ውስጥ በወያኔ ጦር እና በሌሎች የግጭቱ ተካፋዮች የጦር ወንጀል እና በሰው ልጆች ስብእና ላይ የተደረጉ ወንጀሎች መፈጸማቸውን እንደገለጹ ከዚህ በፊት መዘገባችን ይታወሳል።

የግንቦት 7 ድምጽ የወያኔ አገዛዝ ከፍተኛ ባለስልጣናት በሶማሊያ ብቻ ሳይሆን በኦጋዴን፣ በጋምቤላ እና በሌሎችም የአገራችን ክፍሎች ለተካሄዱት የጅምላ ግድያዎች፣ አስገድዶ መድፈር፣ መንደሮችን ማቃጠል እና ሌላም ወንጀሎች ሊከሰሱ እንደሚችሉ እና እነዚህን ወንጀሎችም በተመለከተ ምርመራ እየተደረገባቸው ያሉትን ባለስልጣናት ስም ዝርዝር ማውጣቱ ይታወሳል። ከነዚህም ባለስልጣናት መሃል የወያኔው ቁንጮ መለስ ዜናዊ፣ ቀኝ እጁ በረከት ስምኦን፣ የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር አባይ ጸሃዬ እና ሌሎችም ይገኙበታል።

በተያያዘ ዜና በአኟክ ህዝብ ላይ ባደረገው ጭፍጨፋ በዘር ማጥፋት ወንጀል ሊከሰስ እንደሚችል የታወቀበት ወያኔ፣ የጋምቤላ ህዝብ ድጋፍ እንዲያደርግለት እያስገደደ መሆኑ ተጋለጠ።ጀኖሳይድ ዎች የተባለው የዘር ማጥፋት ወንጀል እንዲጠፋ የሚታገል ድርጅት ለተባበሩት መንግስታት የሰብዓዊ መብት ኮሚሽነር በመለስ መንግስት ላይ ለዘር ማጥፋት ወንጀል ምርመራ እንዲያደርግ እና እርምጃ እንዲወስድ ጥሪ ካቀረበ ወዲህ እየተባባሰ የመጣው የወያኔ ፍርሃት ሞልቶ መፍሰሱን ቀጥሏል።

ቅዳሜ ዕለት የአኟክ ሚዲያ የተባለው የዜና አውታር የጋምቤላ ምንጮችን ጠቅሶ እንደዘገበው፣ የጀኖሳይድ ዎች ጥሪ ከቀረበ ወዲህ ወያኔ በጋምቤላ ድጋፍ ለማሰባሰብ ሽር ጉድ ማለቱን ቀጥሏል። እንደ አውታሩ ዘገባ፣ ባላፈው ሳምንት ወያኔ የድጋፍ ማሰባሰቢያ ደብዳቤ ወደ ጋምቤላ ክልል ህዝብ ተወካዮች ልኮ ሁሉም ፊርማቸውን እንዲያሳርፉበት ትእዛዝ ሰጥቷል። የደብዳቤው አላማም፣ መለስን እና አገዛዙን በጋምቤላ ከተከሰተው በሰው ልጆች ስብእና ላይ የተፈጸመ ወንጀል ተጠያቂነት ለማትረፍ ነው ተብሏል።

ነገር ግን፥ የወደቀ ግንድ ምሣር ይበዛበታል እንዲሉ፥ የህዝብ ተወካዮቹ ወያኔ ሊወድቅ እየተንገዳገደ መሆኑን የተረዱት በሚመስል ሁኔታ በድፍረት "ደብዳቤውን አንፈርምም፤ ይልቁንስ የደብዳቤውን ጸሃፊ ልናውቅ ስለምንፈልግ ይምጣልን" ማለታቸውን አኝዋክ ሚድያ ዘግቧል።

ይህ የፊርማ ማሰባሰብ ሙከራ ስላልተሳካም፣ ድጋፍ አስገድዶ ማግኘት በሚቻልበት ሁኔታ ላይ ለመነጋገር ወያኔ የጋምቤላውን ክልል አስተዳዳሪ ባስቸኳይ ወደ አዲስ አበባ እንዲመጣ ያዘዘው ሲሆን፤ ከምክክሩ በኋላም አኟኮችን እና ሌሎች የጋምቤላ ነዋሪዎችን በማስገደድ ወያኔን በመደገፍ ትዕይንተ ህዝብ እንዲያካሂዱ ለማድረግ መስማማታቸው በዚሁ የዜና አውታር ተዘግቧል።

እንደ አኟክ ሚዲያ ዘገባ፥ ብዙዎች አገዛዙ ሊወድቅ እንደደረሰ ስለሚሰማቸው፣ አስገድዶም ቢሆን ድጋፍ ማግኘቱ እየከበደው መጥቷል። የድጋፍ ማሰባሰብ ዘመቻው አለመሳካት ስላበሳጨውም፣ ሁሌም ወደማይረሳው ዜጎችን በህገ ወጥ መንገድ የማጥቃት ዘመቻ ተመልሶ ሰሞኑን ወደ አስር የሚሆኑ ወጣት አኟኮችን የማይታወቅ ቡድን አባል ናችሁ በማለት ማሰሩን፤ እንዲሁም በዚህ ዘመቻው ቀድሞ የደገፉትና የህዝባቸውን ጭፍጨፋ ያመቻቹት እንኳ እንደማይቀርላቸው እንደሚገመት የዜና አውታሩ ዘግቧል።

የግንቦት 7 ድምጽ ከዚህ ቀደም በዘር ማጥፋት ወንጀል ክስ ሊመሠረትባቸው ይችላል በሚል የወያኔ ባለስልጣናትን ስም ዝርዝር ለህዝብ ይፋ ካደረገበት ጊዜ ጀምሮ በነፍሰ ገዳዮቹ ሸንጎ ከፍተኛ ሽብርና ድንጋጤ መፈጠሩን መዘገባችን ይታወሳል።

## የብአዴን ታጋዮች በተደጋጋሚ አንስተውት የነበረውን የመብት ጥያቄ በማኮልሸት የወያኔ መሪዎችን ላሉበት ትዕቢት ካበቁት ጂሌዎች አንዱ ........................(ከገፅ 1 የዞረ)

የባለቤቱን መታሰር አለቆቹ በጠሩት ስብስባ ላይ ሆኖ የሰማው ተፈራ ዋልዋ እጅግ ከመናደዱ የተነሳ ስብሰባውን አቋርጦ ለመውጣት እንደተገደደ የዘገበው ሪፖርተር ጋዜጣ፣ የወያኔ ብሄራዊ የደህንነት አገልግሎትና የፌደራል ፖሊስ የጋራ ጸረ-ሽብር ግብረሃይል "አከሸፍኩ" ብሎ ሲለፍፍ በሰነበተው መግለጫ እንደገለጸው የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራዉን ሴራ ለረጅም ጊዜ ሲከታተል ከቆየ፣ የወያኔ ትልቁ ሰው ተፈራ ዋልዋ ክብሩን በሚፈታተን መልኩ ሚስቱ ለውርደት እስር ባበቃት ግጭት ውስጥ እንዳትገባ አስቀድሞ ለመከላከል እንዲችል ለምን መረጃ እንዳላገኘ የገለጸው አንዳችም ነገር የለም ፡፡

ይህም በበርካታ ታዛቢዎች ዓይን ከመለስ ዜናዊና በረከት ስምኦን የመሳሰሉ ፈላጭ ቆራጭ የወያኔ ቁንጮዎች በስተቀር ሌሎች ቱባ ባለስልጣናት በአሁኑ ወቅት በአገሪቱ ውስጥ ምን እየተደረገ እንዳለ እንኳ ፍንጭ እንደሌላቸው የሚያመለክት እንደሆነ ፍንጭ ሰጥቶአል ተብሎአል፡፡

ህ በእንዲህ እንዳለ የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት በኢትዮጵያ ስላለው የሰብዓዊ መብት አያያዝ በቅርቡ ያወጣውን ዓመታዊ ሪፖርት በማጣጣል የወያኔ መገናኛ ብዙሃን በሥርዓቱ ቁንጮዎች ልዩ ትዕዛዝ የተቀነባበረ የስድብ ዘመቻ መክፈታቸው ታወቀ።

ወያኔ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተጠናከረበት በመጣው ህዝባዊ ተቃውሞ እየተደናገረና ተስፋ እየቆረጠ በመጣ ቁጥር፣ በድንጋጤ እየወሰደ ያለው የደመነፍስ እርምጃ ባገር ቤት ባሉት ወገኖቻችን ላይ ምን ያህል የከፋ እንደሆነ አምርረው የሚናገሩ ሃይሎች፤ ይባስ ብሎ ላለፉት 18 አመታት አቅፎና ደግፎ ከግብር ከፋዩ ህዝባቸው በሚሰበስቡት ገንዘብ ልገሳ የሥልጣን እድሜውን ካራዘሙለት ምዕራባዊያን፤ ያውም ከልዕለ ሃያሏ አገር አሜሪካ ጋር ለመላተም ስድብ መጀመሩ የተስፋ መቁረጡ ደረጃ ያለበትን ያመለክታል ብለዋል።

ይህንን የአሜሪካ መንግስት የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት በኢትዮጵያ ላይ ያወጣውን የሰብዓዊ መብት አያያዝ ሪፖርት "በውሸት የተሞላ ከንቱ መመጻደቅ" ሲል የስድብ ውርጅብኝ የሚሰነዝረው የወያኔ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት መግለጫ፣ ደርግ ሥልጣን ላይ በቆየባቸው አመታት የቀድሞዋን ሶቬት ህብረት ተማምኖ "በአሜሪካን ኢምፔሪያልዚም" ላይ ያወርድ የነበረውን ስድብና ዛቻ ይመስላል በማለት አንድ አስተያየታቸውን ለግንቦት 7 የአዲስ አበባ ዘጋቢ የሰጡ ዜጋ ተናግረዋል።

### <u>በተወዳጁ ኢትዮጵያዊው ጥላሁን ቀብር ላይ ያልተሳካው ሙከራ - (ከ3ኛው ገፅ የዞረ)</u>

ኢሕአዴግ ይህን አጋጣሚ ተጠቅሞ፣ አቶ በረከትም በውስጣቸው ያለውን የማይጠፋ ጥላቻ አምቀውና አፍነው የፖለቲካ ጠቀሜታ ለማግኘት መጣራቸው የተሳካ መስሏቸው ከሆነ፤ እድሜ እነ አበበ ባልቻ ለሠሩት ቅጥፈት የተሞላበት ሂደት፣ ተንኮሉ ይፋ እንዲወጣ አድርገውት ሕዝብ ታዝቦ ጨርሷል፡፡

ጥላሁን ኢትየጵያዊነትን እንጂ ዘረኝነትን እንኩዋን ሊቀበለው መስማትም ይቀፈው የነበረ ጉዳይ ነውና በምንም መልኩ የኢሕአዴግ ደጋፊ ማድረግ ሊሞከር የማይችል ቅዠት ነው፡፡

በ97 ምርጫ ቅንጅት ለምርጫ ቅስቀሳ ይጠቀምበት የነበረውን «ኢትዮጵያ» የተሰኘውን ዜማውን በፈቃደኝነት ጥቅም ላይ እንዲውል ሲያደርግ፣ ያ ኢሕአዴግን ምን ያህል እንዳሳረረውና እንዳስቆጨው ግልጽ ነበር፡፡ በተደጋጋሚ በተለያየ መልክ ለማስከልከል ተሞክሮም አልተሳካም፡፡ ጥላሁን ስለነጻነት፣ ስለ አንድነት እና ስለ ኢትዮጵያዊነት ተናግሮ አይጠግብም ነበር፡፡ አሁን ታዲያ ለምን ወደ ኢሕአዴግ ካምፕ ለመውሰድና በሱ ቀብር የሕዝብን ፍቅር ለማግኘት ተሞከረ? ይህ ነው መመለስ ያለበት ጥያቄ፡፡

ደግነቱ ሕዝብ አውቆታልና፣ ተረድቶታልና ወደ ኢሕአዴግ የማይረባ ፕሮፓጋንዳ ተስቦ እውነቱን አይሸሽም፡፡ በነገራችን ላይ አበበ ባልቻንም አትፍረዱበት፤ "ውሻ በበላበት ይጮሃል" ነውና በራሱ ውሻነት ታዝቦ መተውና ያ የማይቀር የፍርድ ቀን ሲመጣ እህ ማለት ይሻላል፡፡ ፈጣሪ የጥላሁንን፣ የንጹሁን፣ የቀናውን፣ የዜማ ንጉሱን፣ አዛኝ ርሁሩሁን ሰው ነፍስ በገነት ያሳርፍልን፡፡› ፈጣሪም በትንሣኤው ዕለት ጥላሁንን ኛ ማለቱ ፍቅሩን ሲያሳይ ነውና፡፡


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**

**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

በ17870 KHZ በ 16 ሜትር ባንድ እና በ18350 KHZ በ19 ሜትር ባንድ ላይ የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።



**ውድ አንባቢዎቻችን**

**ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ዎይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን።** g7radio@ginbot7.org